፭/ **"ዝርያ"** ማለት ተመሳሳይ ውጫዊ እና ውስጣዊ ወይም ሥነ ዘረመል ባህርያት ያላቸውና እነዚህንም ባህርያት በተከታታይ ውልደት ማስተላለፍ የሚችሉ የእንስሳት ስብስብ ነው፤

፮/ **"አባላዘር"** ማለት በሰው ቴክኒካዊ አሠራር ከተባዕት እንስሳ ተሰብስቦና በላቦራቶሪ ተቀነባብሮ በቀሰም ውስጥ ወይም በሌላ መሰል ዘዴ የታሸገ የወንዴ ዘር ሲሆን በሰው ቴክኒካዊ አሠራር ከተባዕት እንስሳ ተሰብስቦ በላቦራቶሪ ሳይቀነባበርና በቀሰም ውስጥ ሳይታሸግ ወዲያው አገልግሎት ላይ ሊውል የሚችል የወንዴ ዘርንም ያጠቃልላል፤

፯/ **"ሽል"** ማለት በቤተሙከራ ወይም በእንስት እንስሳ ማህፀን ውስጥ በአባለዘር የለማ እንቁላል ማለት ነው፡፡

፰/ **"የለማ እንቁላል"** ማለት የወንዴና ሴቴ ዘር በመዋሃድ ወደ ሜሬቴትነት ሊለወጥ የሚችል የጾሮ ወይም መሰል የአእዋፍ ዝርያ እንቁላል ነው፤

፱/ **"ማዳቀል"** ማለት በሰው ሰራሽ ወይም በተፈጥሮአዊ ዘዴ ሁለት ዝርያዎችን በማገናኘት የተሻለ ምርታማ የእንስሳ ዝርያ የሚገኝበት ዘዴ ነው፤

፲/ **"የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል"** ማለት በመረጣ ወይም በማዳቀል ወይም ሁለቱን ዘዴዎች በጥምረት በመጠቀም የሚደረግ የእንስሳት ምርታማነት የማሻሻል አሠራር ነው፤

5/ **"Breed"** means a group of animals that have common phenotypic and genotypic characteristics, can be transmitted to the next generations;

6/ **"Semen"** means an ejaculate collected artificially from male reproductive tract and processed and packed in straws or any other form for use in artificial insemination; it also includes fresh ejaculate collected artificially from male animal for immediate use;

7/ **"Embryo"** means a fertilized egg by spermatozoon either invivo or invitro;

8/ **"Fertile Egg"** means cel s resulting from the union of ovum and spermatozoon that develops to embryo;

9/ **"Cross Breeding"** means artificially inseminating or naturally mating of two different breeds to obtain improved genotypes or for research purpose;

10/ **"Livestock Breed Improvement"** means enhancement of animal productivity through selection, cross breeding or both;

፲፩/ **"ግብዓት"** ማለት ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ወይም ለእንስሳት ምርት ማቀናበሪያ የሚውል ስነ-ህይወታዊና ቴክኒካዊ ቁሶችን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚጠቅሙ እንደ የቁም እንስሳት፣ አባለዘር፣ ሽል፣ የለማ እንቁላል፣ ፈሳሽ ናይትሮጂን የስነ-ተዋልዶ ቁሳቁሶች፣ የእንስሳት ምርቶች እና ለእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያ የሚውሉ ውህዶችን የሚያጠቃልል ነው፤

፲፪/ **"መኖ"** ማለት ለእንስሳት ምግብነት እንዲውል የተመረተ ወይም የተቀነባበረና በእንስሳት ጤና ላይ ጉዳት የማያደርስ የእንስሳት ምግብ ነው፤

፲፫/ **"ቴክኖሎጂ"** ማለት አዲስ ወይም የተሻሻለ የአሠራር ዘዴ ሲሆን ጥቅም ላይ ሲውልም የእንስሳት ምርትና ምርታማነት፣ የምርት ጥራት እና የአሠራር ቅልጥፍናን የሚጨምር ነው፤

፲፬/ **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ ፵፯ የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፲፭/ **"ሚኒስቴር"** ወይም **"ሚኒስትር"** ማለት እንደቅደም ተከተሉ የግብርና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲፮/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፤

፲፯/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

11/ **"Input"** means a biological or technical item employed to enhance production and productivity such as live animals, semen, embryo, fertile egg, liquid nitrogen, reproduction equipment, reagents and chemicals for livestock product processing;

12/ **"Feed"** means livestock food produced or processed for the purpose of feeding livestock and that has no health hazard;

13/ **"Technology"** means new tecniques that improve the production and productivity, quality, and efficiency of livestock and livestock product;

14/ **"Region"** means any Region established under Article 47 of the Constitution of The Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes Addis Ababa and Diredawa City Administrations;

15/ **"Ministry"** or **"Minister"** means the Ministry or the Minister of Agriculture respectively;

16/ **"Person"** means natural or juridical person;

17/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

፫. ዋና መስሪያ ቤት

የኢንስቲትዩቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ስፍራዎች ማዕከላትና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ይኖሩታል፡፡

፬. ዓላማ

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ የሀገራችንን እንስሳት ሀብት ዝርያ ምርታማነት፣ ምርት ልማት፣ ጥራትና የገበያ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ አካባቢያዊ ዘላቂነትንና ተደራሽነትን ባረጋገጠ መልኩ ዘርፉ ለኢኮኖሚ ዕድገትና ለሀገር ብልጽግና የላቀ አስተዋጽዖ እንዲያበረክት ማድረግ ነው፡፡

፭. የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የእንስሳት ዝርያዎችን ለማሻሻል፣ ዘላቂ የዝርያ አቅርቦት ለማስፋፋት የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እና የምርት ተዋጽዖ ማቀነባበሪያዎችን ተወዳዳሪ ለማድረግ የሚረዱ ጥናትና ምርምሮችን ያካሂዳል፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግርም ይሠራል፣

፪/ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል እና የእንስሳት ምርትና ተዋጽዖ ሞዴል የምርት ማቀነባበሪያዎችን ያቋቁማል፣ በዘርፉ ያሉ አገር በቀል እውቀቶችን ይለያል፣ እንዲሁም በምርት ማቀነባበር ላይ የተሰማሩ የግል ኢንቨስትመንቶች የምርምር ክፍሎች እንዲያቋቁሙ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣

፫/ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል እና የእንስሳት ምርትና ተዋጽዖ ሁለገብ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ የሚረዱ የፖሊሲ፣ የስትራቴጂ፣ የፕሮግራምና መርሐ ግብሮችን ሀሳብ ያመነጫል፣

3. Head Office

The Institute shall have its Head Office in Addis Ababa and may establish Centers and Branch Offices elsewhere as deemed necessary.

4. Objective

The objective of the Institute shall be to ensure equitable and environmentally sustainable breed productivity, product quality and market competiveness of the livestock sector so as to boost its contribution to the overall economic development and prosperity of the country.

5. Powers and Duties the Institute

The Institute shall have the following Powers and Duties:

1/ Undertake research and studies on livestock breed improvement so as to expand sustainable breed supply, livestock product and by-product processing; works towards technology transfer;

2/ Establish model processing units; identify sectoral indigenous knowledge; renders technical support to livestock product and by-product private investments to establish research units of breed improvement and livestock product processing;

3/ Generate ideas on policies, strategies, programs, and action plans that ensure the overall competiveness of breed improvement and livestock product processing;

፬/ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ ዘመናዊ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ፣ የእንስሳት ምርትና ተዋጽዖ ማቀነባበሪያ እና የእንስሳት እርባታ ግብዓቶችን ወደ ሀገር በማስገባት፣ በሀገር ውስጥም በማምረትና በማባዛት አገልግሎት ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ ግብዓቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስገቡ አካላት የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

፭/ በአገር አቀፍ ደረጃ የዝርያ ማሻሻያ እና የእንስሳት ምርት ማቀነባበርን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ይሠራል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ለክልሎች ድጋፍና ምክር ይሰጣል፤

፮/ ለእንስሳት ዝርያ መሻሻል አስተዋጽዖ የሚያደርጉ የእንስሳት ብዜት ማዕከላትን ያቋቁማል፤ ያደራጃል፤ ይመራል፤ በሀገሪቱን ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች ዝርያ ማሻሻያና ብዜት ማዕከላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤

፯/ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያና ብዜት መረጃ እና የምርትና ተዋጽዖ ማቀነባበሪያ ለማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያ፣ የኢንቨስትመንትና ሌሎች መረጃዎችንና ዕውቀት ያሰባስባል፣ ይተነትናል፣ የመረጃ ቋት ያደራጃል፤ ድረ-ገጽ ያዘጋጃል፤ አመቺ በሆኑ መገናኛ ብዙሃን ያሰራጫል፤

፰/ ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻል እና ምርትና ተዋጽዖ ማቀነባበር የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኒክ፣ የቴክኖሎጂ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን ይሰጣል፤ አውደ ጥናቶችን፣ ሲምፖዚዬሞችን፣ ሴሚናሮችንና የልምድ ልውውጦችን ያዘጋጃል፤

4/ Import, domestically produce and multiply quality and standardized inputs for breed improvement, livestock products and by-product processing and makes it available for use; provide technical support to importers;

5/ Works together with stakeholders at national level on livestock breeding and livestock products processing; advise and support regions whenever necessary;

6/ Establish, organize and lead animal breeding centers that contribute for genetic improvement; collaborate with other breed improvement and multiplication centers in the country;

7/ Collect and analyse technological knowledge, market information, and investment data necessary for breed improvement and livestock product and by-product processing; develop database and webpages; desiminate information through appropriate media;

8/ Provide practical focused trainings, workshops, symposia, seminars, and other tailor-made trainings on technical, technological, management and marketing issues that assists the development and competitiveness of the breed improvement and livestock product processing;

፱/ ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የምርት ማቀነባበር እና የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ተግባራትን ለመደገፍ እንዲቻል በቁርኝት መርሐ ግብር የአቅም ግንባታ ለማከናወን፣ ደረጃውን የጠበቀ ዝርያዎችና ዘር ወደ አገር ውስጥ ለማስገባትም ሆነ ለማስወጣት እና ውጤታማ የግብይት ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤

፲/ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻልን እና እንስሳት ምርትና ተዋጽዖ ማቀነባበርን በተመለከተ በምርት ሂደት እቅድና በጥራት አጠባበቅ ላይ የናሙና ምርት ማምረቻና ላብራቶሪዎች በኢንስቲትዩቱ ውስጥ በማቋቋም ድጋፍና የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፤

፲፩/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል እና እንስሳት ምርትና ተዋጽዖ ማቀነባበር ኢንቨስትመንትን የሚመለከቱ ሥራዎችን በአግባቡ መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፤ የኢንቨስትመንት አማራጮችንና እምቅ አቅሞችን ይለያል፤ የኢንቨስትመንት ሥራዎች የሚስፋፉበትን ስልት ይቀይሳል፤

፲፪/ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል፣ እንስሳት ምርትና ተዋጽዖ እና የመኖ ማቀነባበር ላይ ለሚሠማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት የማማከርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

9/ Works together with pertinent stakeholders on twinning capacity building programs, on importation and exportation of standard breeds and genetic materials and on establishement of effective market system so as to enable the livestock product processing and genetic improvement to attain international standard;

10/ Provide support and advisory services to livestock breed improvement and livestock product processing on production process plan, and quality compliance by establishing sample production laboratories and model processing plant in the institute;

11/ In collaboration with other stakeholders, ensure proper organization of breed improvement and product processing investement activities, identify potential investment capacity of the sector, devise mechanism for proper investment promotion and work towards the effectiveness of the investments;

12/ Advice and give technical support for investors who wish to engage in breed improvement, livestock product and product processing and livestock feed processing in the selection of technology, negotiation, construction, installation and product testing;

## ፰. ምክትል ዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር

ምክትል ዋና ዳይሬክተር የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

፩/ የሚመደብበትን የሥራ ዘርፍ ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

፪/ በዋና ዳይሬክተር ተለይተው የሚሰጠውን ተግባራት ያከናውናል፤

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለይቶ ባልወከለበት ወቅት በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተክቶ ይሰራል፡፡

## ፱. በጀት

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግስት ከሚመደብ ይሆናል፡፡

## ፲. የሒሣብ መዛግብት

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሒሣብ መዛግብት ይይዛል፤

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሒሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በውስጥ ኦዲተርና በፌደራል ዋናው ኦዲተር ይመረመራል፡፡

## 8. Powers and Duties of the Deputy Director General

The Deputy Director General shall have the Following Powers and Duties:

1/ Leads and administers the department assigned;

2/ Performs tasks assigned by the Director General;

3/ Unless the Director General delegates otherwise, the senior Deputy Director General in appointment shall act on behalf of the Director General in his absence.

## 9. Budget

Budget of the Institute shall be allocated by the Government.

## 10. Books of Accounts

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of accounts;

2/ The books of accounts and other financial documents of the institute shall be audited by internal auditor and Federal Auditor General.

**፲፩. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሚያዚያ ፮ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

ዓብይ አህመድ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

**11. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazetee.

**Done at Addis Ababa, On this 14th Day of April, 2022**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**